የ/ሰ/መ/ቁ. 114623

ቀን 22/06/2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

አይሸሹም መለሰ

ፀሃይ መንክር

አመልካችዎች፡- 1. ሀጅ ቢያ አባመጫ

2. አቶ ከሊፋ አባ ቆያስ } ጠበቃ ከድር መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. የኦሮሚያ ክልል ደንና ዱር አራዊት ድርጅት አልቀረበም

2. መራዋ አርሶ አደሮች የህብረት ሥራ ማህበር ጠበቃ በላይ እሸቱ ቀረቡ

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካችዎች ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር የእርቅ ሥምምነት በማድረግ በፍርድ ቤት እንዲመዘገብና እንዲፀድቅ ካደረጉ በኃላ አንደኛ ተጠሪ ያቀረበውን የፍርድ መቃወሚያ በመቀበል የእርቅ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ውሳኔ የሰጠው በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም ?የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው ጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡
2. አመልካችዎችና ሁለተኛው ተጠሪ በፈረንጅ ዕድ ሽያጭ ውል በተመለከተ ባለመስማማታቸው አመልካቾች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች ከሳሽ፣ሁለተኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመከራከር ላይ እያሉ ጥር 5 ቀን 2001ዓ.ም ባደረጉት ዕርቅ ውል አመልካችዎች 1,200,000 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ብር) ለሁለተኛ ተጠሪ ሊከፍሉ ሁለተኛ ተጠሪም የክርክሩ መነሻ የሆነውን የፈረንጅ ዕድ ለአመልካችዎች ሊያስረክቡ ሥምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡ አመልካችዎችና ሁለተኛ ተጠሪ የዕርቅ ሥምምነታቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

አቅርበው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14220 ህዳር 25 ቀን 2002ዓ.ም በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277(1) መሠረት የዕርቅ ውላቸውን በመቀበል ግራቀኝ በዕርቅ ውሉ መሠረት እንደፈፅሙ ትዕዛዝ በመስጠት መዝገቡን ዘግቶታል ።

3. አንደኛ ተጠሪ አመልካችዎችና ሁለተኛው ተጠሪ ጥር 5 ቀን 2001ዓ.ም አድርገነዋል በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ህዳር 25 ቀን 2002ዓ/ም ያፀደቁት የዕርቅ ውል የፈፀሙበት የፈረንጅ ፅድ የመንግስት ደን መሆኑን ገልፆ የዕርቅ ውሉ ፈራሽ ነው እንዲባልለት ጥር 27 ቀን 2005ዓ/ም የተፃፈ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርቧል። የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳያቸውን በዕርቅ ያዘጉት አመልካችዎችና ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ አንደኛ ተጠሪ ፍርዱን ለመቃወም የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የዕርቅ ስምምነቱ የፍርድ መቃወሚያ አመልካችን መብት የሚነካ በመሆኑ የዕርቅ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል።

4. አመልካችዎች ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል። ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የፍርድ መቃወሚያ አቅርበው የዕርቅ ስምምነት በተደረገበት የፈረንጅ ፅድ ላይ መብት የሌለው መሆኑ በወቅቱ በተያዘው ቃለጉባኤ የተረጋገጠ ስለሆነ ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዕርቅ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል። አንደኛ ተጠሪ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል ። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የዕርቅ ውል የተደረገበት የፈረንጅ ፅድ የመንግስት ደን በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዕርቅ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል።

5. አመልካችዎች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ እኛ የገዛነው የመንግስት ደን ሣይሆን የሁለተኛ ተጠሪ ንብረት የሆነ የፈረንጅ ፅድ ነው። አንደኛ ተጠሪ ከሻጭ ጋር ያለንን ልዩነት በዕርቅ ጨርሰን የዕርቅ ውሉ በፍርድ ቤት ከፀደቀ በኃላ ማስረጃ እንዲፃፍ በማድረግ የዕርቅ ውሉ እንዲፈርስ ማድረጉ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር ታይቶ እንደታረምልኝ በማለት አመልክተዋል ። 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ንብረቴን ነው የሸጥኩት ከአመልካችዎች ጋር የዕርቅ ውል የፈፀምኩት በንብረቴ ላይ በመሆኑ የሁለተኛ ተጠሪ የፍርድ መቃወሚያ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የአመልካችዎችን የሰበር አቤቱታ በመደገፍ መልስ ሰጥቷል ። አንደኛ ተጠሪ ግራቀኙ ዕርቅ የፈፀሙበት የመንግስት ደን በመሆኑ የአመልካችዎች የሰበር አቤቱታ

ተቀባይነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል ፡፡ አመልካችዎች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል ፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ሁለት ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት የሚከራከሩበትን ጉዳይ በዕርቅ መጨረስ እንደሚችሉና የእርቅ ውሉን ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት አቅርበው ማፀደቅ እንደሚችሉ ፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀ የዕርቅ ውል ሥምምነት በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ያህል አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 276 እና አንቀፅ 277(1) ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

7. አመልካችዎችና ሁለተኛው ተጠሪ የፈረንጅ ፅድ ሽያጭ ውል በተመለከተ ጥር 5 ቀን 2001ዓ.ም ያደረጉትና ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277(1) መሠረት ያፀደቁት የዕርቅ ውል የፍርድ ያህል አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው በመሆኑ በዚህ ዕርቅ ውል ተካፋይ ያልሆነ መብቴ ተነክቷል የሚለው አንደኛ ተጠሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዕርቅ ውሉን በማፅደቅ የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት ፤የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ማቅረቡና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአንደኛ ተጠሪን የፍርድ መቃወሚያና ማመልከቻን ማስረጃ በመቀበል የዕርቅ ውሉ የመንግስት ደን የሚያስተዳድረውን የአንደኛ ተጠሪን መብትና ጥቅም የሚነካ በመሆኑ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሥነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

8. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አንደኛ ተጠሪ የፍርድ መቃወሚያ ለማቅረብ መሠረትና ማስረጃ የሆነውንና አመልካችዎች ከሁለተኛው ተጠሪ ጋር የዕርቅ ሥምምነት የፈፀሙበት የፈረንጅ ፅድ ጫካ የመንግስት ደን መሆኑን የሚያረጋግጠውን የቴክኒክ ኮሚቴ ሪፓርትና ማስረጃ ያለበቂ ምክንያት ውድቅ በማድረግ አከራካሪው የፈረንጅ ፅድ ዛፍ ጫካ በጨረታ ለአመልካችዎች ከመሸጡ በፊት የተያዘውን ቃለ ጉባኤ ነው መያዝ ያለበት በማለት አከራካሪው የፅድ ዛፍ የሁለተኛ ተጠሪ ሀብት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የማስረጃ አመዛዘን መርህን ያልተከተለና መሠረታዊ የማስረጃ ህግ ድንጋጌዎችን የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 250 እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136(1) ያልተከተለና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመገንዘብ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም ፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችዎች እና አንደኛ ተጠሪ የዕርቅ ሥምምነት ያደረጉት የአንደኛ ተጠሪ መብትና ጥቅም ባለበት የመንግስት ደን ላይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቦለት እያለ

አንደኛ ተጠሪ የዕርቅ ሥምምነቱን መቃወምና ፈራሽ ለማስደረግ የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለውም በማለት የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 184867 መጋቢት 14 ቀን 2007ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

# ንብረት